


# +++ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ +++

# የዕለት እንጀራ

ሚያዝያ ፬ **ማቴዎስ ፳፩፡ ፩-፲** ፳፻፩




የዐቢይ ጾም እያንዳንዱ ሳምንት (እሁድ) ከጌታችንና አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርትና ስራ ጋር በተያያዘ ስም ተስጥቶት ተከፍሏል:: ይህ ሳምንት **ሆሳዕና** ይባላል:: ሆሳዕና ማለት ”መድኃኒት መባል ይገባዋል” ማለት ነው።

አሁንስ፥ ይላል
እግዚአብሔር፥
በፍጹም
ልባችሁ፥
በጾምም፥
በልቅሶና በዋይታ
ወደ እኔ
ተመለሱ።
ልባችሁን እንጂ
ልብሳችሁን
አትቅደዱ
ኢዩ፪:፲፪-

አምላካችሁም
እግዚአብሔር
ቸርና መሐሪ፥
ቍጣው የዘገየ፥
ምሕረቱም የበዛ፥
ለክፋትም
የተጸጸተ ነውና
ወደ እርሱ
ተመለሱ።
ኢዩ ፪: ፲፫

ወደ ኢየሩሳሌምም ቀርበው ወደ ደብረ ዘይት ወደ ቤተ ፋጌ ሲደርሱ፥ ያን ጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከ፥ እንዲህም አላቸው:- በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥ በዚያን ጊዜም የታሰረችን አህያ ውርንጫም ከእርስዋ ጋር ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ።

ማንም አንዳች ቢላችሁ:- **ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ፤ ወዲያውም ይሰዳቸዋል**።

ለጽዮን ልጅ :- እነሆ፥ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉአት ተብሎ በነቢይ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ።

**ደቀ መዛሙርቱም ሄደው ኢየሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ፥** አህያይቱንና ውርንጫዋንም አመጡለት፥ **ልብሳቸውንም በእነርሱ ላይ ጫኑ፥** ተቀመጠባቸውም።

**ከሕዝቡም እጅግ ብዙዎች ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፥** ሌሎችም ከዛፍ ጫፍ ጫፉን እየቈረጡ በመንገድ ላይ ያነጥፉ ነበር።

የሚቀድሙትም ሕዝብ የሚከተሉትም:- **ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ ሆሣዕና በአርያም** እያሉ ይጮኹ ነበር።

ወደ ኢየሩሳሌምም በገባ ጊዜ **መላው ከተማ:- ይህ ማን ነው? ብሎ ተናወጠ**።

## በዚህ ዕለት ከሚታሰቡት መካከል፡

ሆሳዕና (ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምስጋና ታጅቦ ወደ ኢየሩሳሌም መግባት)

### ምስባክ

እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት
አስተዳሎከ ስብሐተ በእንተ ጸላዒ
ከመ ትንሥቶ ለጸላዒ ወለገፋዒ

መዝ. ፰ :፪

### ትርጉም

ከሕፃናትና ከሚጠቡ ልጆች አፍ
ምስጋናን አዘጋጀህ ስለ ጠላትህ ፥
ጠላትንና ቂመኛን ለማጥፋት።